# የስፖርት ማህበራት ስለሚቋቋሙበት ሁኔታ ለመወሰን ተሻሽሎ የወጣ መመሪያ

መስከረም 2011 ዓ.ም.

## መግቢያ

በአገራችን ህዝባዊ መሰረት ያለው ስፖርት ለማንባትና ከስፖርት ሊገኝ የሚችለውን ኢኮኖሚያዊ፣ማህበራዊና ፖለቲካዊ ፋይዳዎችን ወደ ላቀ ደረጃ በማሸጋገር የመላውን ህዝብ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ይቻል ዘንድ ብሄራዊ የስፖርት ፖሊሲ በ1990 ተቀርጾ ላለፉት ሃያ ዓመታት ተግባራዊ ሲሆን ቆይቷል፡፡

በፖሊሲው እንደተመለከተው የስፖርት ማህበራት በተደራጀ አግባብ ስፖርቱን በባለቤትነት የመምራት ኃላፊነት የተጣለባቸው በመሆኑ በአሁኑ ጊዜ ኦሎምፒክ ኮሚቴን ጨምሮ በየስፖርቱ ዓይነቱ አገር አቀፍ ስፖርት ማህበራት ተደራጅተው በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛሉ፡፡

የስፖርት ማህበራቱ የሚመሩትን ስፖርት ለማስፋፋትና ለማሳደግ በሚያደርጉት እንቅስቃሴ በአንድ በኩል የዓለም አቀፍ ስፖርት ማህበራት ህግጋትን አክብረው የመስራት ግዴታ ያለባቸው ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የመንግስትን ፖሊሲና ህግ የማክበርና የመተግበር እንዲሁም በራሳቸው ጠቅላላ ጉባኤ በሚጸድቁ መተዳደሪያ ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት መተዳደር አሠራራቸውን ግልጽና ጠያቂነት ያለው እንዲሆን ማድረግና በዚያው መምራት ይጠበቅባቸዋል፡፡

በ2003 ዓ.ም የስፖርት ማህበራት ስለሚቋቋሙበት ሁኔታ ለመወሰን የወጣው መመሪያ አገር አቀፍ ስፖርት ማህበራት ተገቢውን መስፈርት አሟልተው ተመዝግበውና እውቅና አግኝተው እንዲንቀሳቀሱ ያስቻለ ቢሆንም በመመሪያው ላይ ማሻሻል የሚገባቸው፣መካተት ያለባቸው፣ግልጽነት ሊኖራቸው የሚገቡ ጉዳዮች በመኖራቸው የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር ይህንን የስፖርት ማህበራት ስለሚቋቋሙበት ሁኔታ ለመወሰን የወጣውን መመሪያ አሻሽሎ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

## 1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ መመሪያ"የስፖርት ማህበራት ስለሚቋቋሙበት ሁኔታ ለመወሰን ተሻሽሎ የወጣ መመሪያ ቁጥር 75/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. <u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ወስጥ፡-

1. "ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር "ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ በአዋጅ ቁጥር 916/2008 የተቋቋመ የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ማለት ነው፡፡
2. "የስፖርት ማህበራት" ማለት በዚህ መመሪያ መሠረት የአገር አቀፍ የስፖርት ፌደሬሽን"፣የኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ኮሚቴ፣የኢትዮጵያ ፓራሊምፒክ ኮሚቴ፣የኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸዉ ስፖርቶች ፌደሬሽን፣ የኢትዮጵያ ዩኒቨርስቲዎች ስፖርት ማህበር`፣የኢትዮጵያ ጤና ስፖርት ማህበር፣ የስፖርት አሶሴሽን፣ የስፖርት ክለብ እና ሌሎች ተመሳሳይ ማህበራትን ይጨምራል፡፡
3. "የኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ኮሚቴ" ማለት በኢንተርናሽናል ኦሎምፒክ ኮሚቴ ቻርተር መሠረት በስፖርት ፌደሬሽኖች እና በባለድርሻ አካላትአባልነት የተቋቋመና በዓለም አቀፍ ኦሎምፒክ ኮሚቴ ተመዝግቦ በሚኒስቴሩ ዕውቅና የተሰጠው ማህበር ነው፡፡
4. "የስፖርት ፌደሬሽን" ማለት አንድን ስፖርት በመላ አገሪቱ ለማስፋፋት፣ለማስደግና ለማስተዳደር ከሚኒስቴሩ ፈቃድ ተሰጥቶት የተቋቋመ ማህበር ነው፡፡
5. "የኢትዮጵያ ፓራሊምፒክ ኮሚቴ" ማለት የፓራሊምፒክ ስፖርቶችን በመላ አገሪቱ ለማስፋፋት፣ለማስደግና ለማስተዳደር ከሚኒስቴሩ ፈቃድ ተሰጥቶት የተቋቋመ ማህበር ነው፡፡
6. "የኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸዉ ስፖርቶች ፌደሬሽን" ማለት በመላ አገሪቱ መስማት የተሳናቸው የህብረተሰብ ክፍሎች የሚሳተፉባቸውን ስፖርቶች ለማስፋፋት፣ለማስደግና ለማስተዳደር ከሚኒስቴሩ ፈቃድ ተሰጥቶት የተቋቋመ ማህበር ነው፡፡
7. "የስፖርት አሶሴሽን" ማለት በአንድ የስፖርት ዓይነት ከአምስት ክልሎች በታች የሚዘውተር ስፖርት ሆና ስፖርቱን ለማስፋፋት፣ለማስደግና ለማስተዳደር ከሚኒስቴሩ ፈቃድ ተሰጥቶት የተቋቋመ ማህበር ነው፡፡
8. "የኢትዮጵያ ዩኒቨርስቲዎች ስፖርት ማህበር" ማለት በኢትዮጵያ ወስጥ የሚገኙ የመንግስትና የግል ዩኒቨርስቲዎችን ያካተተ የስፖርት ልማትን ፌስቲቫሎችን፣ ወድድሮችን የሚያስተባብር ሆኖ ከሚኒስቴሩ ፈቃድ ተሰጥቶት የተቋቋመ ማህበር ነው፡፡

9. "የኢትዮጵያ የጠና ስፖርት ማህበር"ማለት ህብረተሰቡ በጤና ስፖርት ያለዉን ተሳትፎና ተጠቃሚነት ለሚጋገጥ በአገሪቱ የጠና ስፖርትን ለማስፋፋት፣ለማስደግና ለማምራት ከሚኒስቴሩ ፈቃድ ተሰጥቶት የተቋቋመ ማህበር ነው፡፡

10. "የስፖርት ክለብ" ማለት የስፖርት እንቅስቃሴን ለሚራመድ የተቋቋመ እና ከሚመለከተው ህጋዊ አካል የምስክር ወረቀት ያገኘ ማህበር ነው፡፡

11. "ኢመርጀንሲ ኮሚቴ" ማለትበሁለት የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ስብሰባዎች መካከል አስቸኳይ ጉዳዮችን አከናወኖ በማቀጥለው ስብሰባ አቅርቦ የሚያስወስን በጠቅላላ ጉባኤው አማካኝነት ከስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት መካከል የሚሰየም አካል ነው፡፡

12. "የውጭ አባላት" ማለት በውጭ ሀገራት የሚኖሩ በተለያዩ የስፖርት ዓይነቶች ሀገራቸውን በግልና በማህበር ወክለው ለመወዳደር የሚፈልጉና በአገር አቀፍ ፌዴሬሽኑ የተመዘገቡ አባላት ወይም አካላት ናቸው፡፡

13. "የክልል/ከተማ አስተዳደር/ ስፖርት ማህበር" ማለት በክልሉ/ከተማ አስተዳደሩ/ ወስጥ አንድን ስፖርት ለማስፋፋት፣ለማስደግና ለመምራት በክልሉ/ከተማ አስተዳዳሩ አግባብ ባለው የክልል አካል ፈቃድ ያገኘ የስፖርት ማህበር ነው፡፡

14. "አባል" ማለት በሀገር አቀፍ ስፖርት ተቋሙ ጠቅላላ ጉባኤ አባል እንዲሆን ተቀባይነት ያገኘ አካል ወይም ግለሰብ ነው፡፡

15. "ሰው" ማለት ማንኛወም የተፈጥሮ ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

16. "ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ" ማለት አንድን ሀገር አቀፍ የስፖርት ማህበር ለመምራት በጠቅላላ ጉባኤ የሚሚጥና ስፖርት ማህበሩን ሥራ በበላይነት የሚያስፈጽም አካል ነው፡፡

17. "ታዋቂ የስፖርት ድርጅቶች"ማለት የትምህርት ሚኒስቴር፣የመከላከያ ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ ሠራተኞች ኮንፌደሬሽን፣ የፌድራል ፖሊስ ኮሚሽን፣ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ማለት ሲሆን በስሩ የሚገኙ የስፖርት ልማት፣ ፌስቲቫሎችና ወድድሮችን የሚያስተባብሩ አካል ናቸው፡፡

## 3. <u>የፆታ አገላለፅ</u>

በዚህ መመሪያ ወስጥ በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትም ፆታ ያካትታል፡፡

## 4. <u>ዓላማ</u>

የመመሪያው ዋና ዓላማ አገር አቀፍ የስፖርት ማህበራት የስፖርት ፖሊሲ፣ዓለም አቀፍና አገር አቀፍ ህግና ደንቦች ተከብረወና ተግባር ላይ ወለው በዘር፣ በፆታ፣ በሃይማኖት፣ በጎሣ እና በፖለቲካ

ልዩነት ሳይደረግ የአገሪቱን ስፖርት በማስፋፋትና በማሳደግ ግልፅነትና ተጠያቂነት ያለው አሠራር ሰፍኖ ህብረተሰቡ በዘርፉ እኩል ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ ነው፣

## 5. ዓርማ

እያንዳንዱ አገር አቀፍ ህዝባዊ የስፖርት ማህበር "ኢትዮጵያ" >> የሚል ቃል በማስቀደም በሚሠራው የስፖርት ዓይነት ይጠራል::

## 6. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በሁሉም አገር አቀፍ ስፖርት ማህበራት ዘንድ ተፈጻሚነት ይኖረዋል::

## 7. ጽ/ቤት

የአገር አቀፍ የስፖርት ማህበራት የራሳቸው ጽ/ቤት በአዲስ አበባ ከተማ ይኖራቸዋል::

# ክፍል ሁለት

## የስፖርት ማህበራት ስለሚመሠረቱበት

## 8. አገር አቀፍ የስፖርት ፌዴሬሽን ስለመመሥረት :-

በአንድ የስፖርት ዓይነት አንድ አገር አቀፍ የስፖርት ማህበር ብቻ የሚመሠረት ሆኖ፣ ህጋዊ ዕውቅና ለማግኘት የሚከተሉትን መመዘኛዎች ማሟላት ይኖርበታል::

1. በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 16 የተጠቀሰትን የጠቅላላ ጉባኤ አባላት ማካተቱ ሲረጋገጥ፣
2. በስፖርት ዓይነቱ ተመዝግበወና ከክልሉ/ከተማ አስተዳደሩ ፈቃድ አግኝተው የተቋቋሙ

   ቢያንስ በ5 የክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ፌዴሬሽኖች በአባልነት ሲኖሩና እያንዳንዳቸው ቢያንስ በወድድር ላይ ያሉ 5 ክለቦች ያላቸው መሆኑ ሲረጋገጥ፣
3. በስፖርት አይነቱ በአገር አቀፍ ደረጃ ወድድሮችን ለመምራት የሚችሉ ከ10-15 ዳኞች ያላቸው መሆኑ ሲረጋገጥ፤
4. በስፖርት አይነቱ የሰለጡኑ ከ10-15 አሰልጣኞች ያላቸው መሆኑ ሲረጋገጥ
5. ጽ/ቤት ያሏቸው መሆኑ ሲረጋገጥ፣

6. በራሳቸው/በማንግስት/በህዝብ/ተሳትፎ የገነቡዋቸው ወይም በኪራይ ያገኙዋቸው የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎች ያሉአቸው መሆኑ ሲረጋገጥ፣
7. አገር አቀፍ የስፖርት ማህበራት ስለሚቋቋሙበት ሁኔታ ለመወሰን የወጣውን ይህንን እንዲሁም በስፖርት ዓይነት ያለውን ዓለም አቀፍ ደንብ መሠረት በማድረግ የራሱን መተዳደሪያ መመሪያ በማውጣት በጠቅላላ ጉባኤ የፀደቀ ጹሁፍ ሲያቀርብ

## 9. የኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ስለመመስረት

በአገሪቱ ወስጥ የሚመሠረተው የኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ኮሚቴ አንድ ብቻ ሆኖ፣ ሕጋዊ ዕወቅና ለማግኘት የሚከተሉትን መመዘኛዎች ማሟላት አለበት፡ –

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 17 የተጠቀሱትን የጠቅላላ ጉባኤ አባላት ማካተቱ ሲረጋገጥ፣
2. በኢንተርናሽናል ስፖርት ፌዴሬሽኖች ወይም አሶሴሽኖች የተመዘገቡና እወቅና ያገኙ ስፖርቶቻቸው በኦሎምፒክ ጨዋታዎች የሚዘውተር ከ5 ያላነሱ ብሔራዊ የስፖርት ፌዴሬሽኖች በአባልነት ተመዝግበው መኖራቸው ሲረጋገጥ ፣
3. ጽ/ቤት ያሉት መሆኑ ሲረጋገጥ፣
4. ይህንን መመሪያ እንዲሁም የኦሎምፒክ ቻርተርን መሰረት በማድረግ የራሱን መተዳደሪያና የአሠራር ስርዓት በማውጣት በጠቅላላ ጉባኤ የጸደቀ ጹሁፍ ሲያቀርብ

## 10. የኢትዮጵያ ፓራሊምፒክ ኮሚቴ ስለመመስረት

በአገሪቱ ወስጥ የሚመሠረተው የኢትዮጵያ ፓራሊምፒክ ኮሚቴ አንድ ብቻ ሆኖ፣ ሕጋዊ ዕወቅና ለማግኘት የሚከተሉትን መመዘኛዎች ማሟላት አለበት፡ –

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 18 የተጠቀሱትን የጠቅላላ ጉባኤ አባላት ማካተቱ ሲረጋገጥ፣
2. በኢትዮጲያ ፓራሊምፒክ ኮሚቴ ተመዝግበው ዕወቅናያገኙ በስፖርት ዓይነት ወይም በጉዳት ዓይነት የተቋቋሙ ከሚኒስቴሩ ፈቃድ የተሰጣቸው፣ ከአቻ የኢንተርናሽናል ስፖርት ፌዴሬሽን ተመዝግበው ዕወቅና ያላቸው ከ5 ያላነሱ ብሄራዊ ፌዴሬሽኖችን በአባልነት ያካተተ መሆኑ ሲረጋገጥ፣
3. የፓራሊምፒክ ስፖርቶች ማህበር መመስረታቸው ሲረጋገጥ፣ እና እያንዳንዳቸው ቢያንስ በወድድር ላይ ያሉ 5 ክለቦች ያሉዋቸው መሆኑ ሲረጋገጥ፣
4. በክልል ወይም ከተማ አስተዳደር የተቋቋሙ ቢያንስ 5 የፓራሊምፒክ ኮሚቴዎች መመስረታቸው ሲረጋገጥ፣ እና እያንዳንዳቸው ቢያንስ በወድድር ላይ ያሉ 5 ክለቦች ያሉዋቸው መሆኑ ሲረጋገጥ፣
□
5. በእያንዳንዱ የአካል ጉዳተኞች በሚስተፉባቸው የስፖርት አይነቶች ከ10–15 አሠልጣኞችና ዳኞች መኖራቸው ሲረጋገጥ፣
6. ጽ/ቤት ያሉት መሆኑ ሲረጋገጥ፣

7. በጠቅላላ ጉባኤ የፀደቀ የመመስረቻ ጹሑፍና የመተዳደሪያ ደንብ ያለው መሆኑ ሲረጋገጥ ሊመሰረት ይችላል::

## 11.የኢትዮጲያ መስማት የተሳናቸዉ ስፖርቶች ፌደሬሽን ስለመመስረት

በአገሪቱ ወስጥ የሚመሠረተው የኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸው ስፖርት ፌደሬሽን አንድ ብቻ ሆኖ፣ ሕጋዊ ዕወቅና ለማግኘት የሚከተሉትን መመዘኛዎች ማሟላት አለበት፡ -

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 19 የተጠቀሱትን የጠቅላላ ጉባኤ አባላት ማካተቱ ሲረጋገጥ፣
2. በክልል ወይም ከተማ አስተዳደር የተቋቋሙ ቢያንስ 5 መስማት የተሳናቸዉ ስፖርቶች ፌዴሬሽን መመስረታቸው ሲረጋገጥ፣ እና እያንዳንዳቸው ቢያንስ በወድድር ላይ ያሉ 5 ክለቦች ያሉዋቸው መሆኑ ሲረጋገጥ፣
3. በእያንዳንዱ መስማት የተሳናቸው በሚተፉባቸው የስፖርት አይነቶች ከ10-15 አሠልጣኞችና ዳኞች ያላቸው መሆኑ ሲረጋገጥ፣
4. ጽ/ቤት ያለው መሆኑ ሲረጋገጥ፣
5. በጠቅላላ ጉባኤ የፀደቀ የመመስረቻ ጹሑፍና የመተዳደሪያ ደንብ ያለው መሆኑ ሲረጋገጥ ሊመሰረት ይችላል::

## 12. የኢትዮጲያ ዩንቨርስቲዎች የስፖርት ማህበር ስለመመስረት

በአገሪቱ ወስጥ የሚመሠረተው የኢትዮጵያ ዩንቨርስቲዎች የስፖርት ማህበር አንድ ብቻ ሆኖ፣ ሕጋዊ ዕወቅና ለማግኘት የሚከተሉትን መመዘኛዎች ማሟላት አለበት፡ -

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 20 የተጠቀሱትን የጠቅላላ ጉባኤ አባላት ማካተቱ ሲረጋገጥ፣
2. በኢትዮጵያ ወስጥ ካሉት ዩንቨርስቲዎች ከግማሽ በላይ የሚሆኑትን በአባልነት የተመዘገቡ መሆኑ ሲረጋገጥ፣
3. በራሳቸው/ከመንግስት/በሕዝብ/ተሳትፎ የገነቡዋቸው ወይም በኪራይ ያገኙዋቸው የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎች ያሉአቸው መሆኑ ሲረጋገጥ፣
4. ጽ/ቤት ያሉት መሆኑ ሲረጋገጥ፣
5. በጠቅላላ ጉባኤ የፀደቀ የመሥራቺ ጹሑፍና የመተዳደሪያ ደንብ ያላቸው መሆኑ ሲረጋገጥ ሊመሠረት ሲችል::

## 13.የኢትዮጵያ የጠና ስፖርት ማህበር ስለመመስረት፣

በአገሪቱ ወስጥ የሚመሠረተው የኢትዮጵያ የጠና ስፖርት ማህበር አንድ ብቻ ሆኖ፣ ሕጋዊ ዕወቅና ለማግኘት የሚከተሉትን መመዘኛዎች ማሟላት አለበት፡ -

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 21 የተጠቀሱትን የጠቅላላ ጉባኤ አባላት ማካተቱ ሲረጋገጥ፣
2. ቢያንስ በ5 ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የተደራጁ የጠና ስፖርት ማህበራት መኖራቸው ሲረጋገጥ፤
3. በራሳቸው፣ ከመንግስት፣ በሕዝብ ተሳትፎ የገነቡዋቸው ወይም በኪራይ ያገኘዋቸው የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎች ያሉአቸው መሆኑ ሲረጋገጥ፣
4. ጽ/ቤት ያሉት መሆኑ ሲሆኑ፣
5. በጠቅላላ ጉባኤ የፀደቀ የመሟሂቻ ጹሑፍና የመተዳደሪያ ደንብ ያላቸው መሆኑ ሲረጋገጥ ሊመሠረት ሲችል፡፡

## 14.<u>የስፖርት አሶሴሽን ስለመመስረት</u>፡ -

በአገሪቱ ወስጥ በአንድ የስፖርት ዓይነት አንድ አገር አቀፍ አሶሴሽን ብቻ የሚሠረት ሆኖ፣ ሕጋዊ ዕወቅና ለማገኘት የሚከተሉትን መመዘኛዎች ማሟላት አለበት፡፡

1. በስፖርቱ ዓይነት ተመዝግበወና ፈቃድ አግኝተው ከ5 ክልሎች በታች የተቋቋሙ የስፖርት አሶሴሽኖች መኖራቸው ሲረጋገጥ፣
2. ቢያንስ የተመዘገቡ 250 አባላት ያላቸው መሆኑ ሲረጋገጥ፣
3. ደረጃቸውን የጠበቁ የመወዳደሪያና የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎች ያላቸው ሚሆኑ ሲረጋገጥ፣
4. ጽ/ቤት ያለው መሆኑ ሲረጋገጥ፣
5. በጠቅላላ ጉባኤ የፀደቀ የመመስረቻ ጹሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ ሲኖራቸው፣
6. ቢያንስ 10 ዳኞችና 5 አሠልጣኞች ሲኖራቸው መመሟሂት ይችላሉ፡፡

## 15.<u>የስፖርት ማህበራት የሚኖሩት አቋም</u>፡ -

የስፖርት ማህበራት አቋም እንደሚከተለው ይሆናል ፡፡

1. ጠቅላላ ጉባኤ፣
2. በጠቅላላ ጉባኤ የተሚረጠ ኦዲተር፣
3. ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ፣
4. ኢሜርጀንሲ ኮሚቴ,፣
5. አግባብነት ያላቸው ቋሚ ንዑሳን ኮሚቴዎች
6. ጽ/ቤት፣

## ክፍል ሦስት

## ስለ ስፖርት ማህበራት አሜራር ጥንቅር፣ ሥልጣንና ተግባር

### 16. የፌዴሬሽኖች ጠቅላላ ጉባኤ ጥንቅር

የፌዴሬሽኖች ጠቅላላ ጉባኤ የሚከተሉትን በአባልነት ማካተት ይኖርበታል፡፡

1. የክልል/ከተማ አስተዳደር የስፖርት ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንቶች ወይም ተወካዮች፤
2. የፌዴሬሽኑ ፕሬዚዳንትና የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ኮሚቴ አባላት፤
3. አገር አቀፍ ፌዴሬሽኖች በባለቤትነት የሚያወዳድራቸው ክለብ ፕሬዚዳንቶች ወይም ተወካዮች፤
4. በሀገር አቀፍ ፌዴሬሽኖች ደረጃ በየስፖርት ዓይነቱ የተቋቋሙ የዳኞች ታዛቢ፣ የአሰልጣኞች አትሌቶች ማህበር ፕሬዚዳንቶች፤
5. በጠቅላላ ጉባኤ የተሚረጡ ለስፖርቱ አስተዋጽኦ ያደረጉ ወይም በስፖርቱ የተለያየ አሜራር በማጡጠት ያገለገሉ የክብር አባላት /ያለደምጽ/፣
6. የኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ኮሚቴ ተወካይ/ያለደምጽ/፣
7. በጠቅላላ ጉባኤ የተሚረጠ ኦዲተር/ያለደምጽ/፣
8 የፌዴሬሽኑ ጽ/ቤት ኃላፊ/ያለደምጽ/፣
9. የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር ተወካይ/ያለደምጽ/፣

### 17. የኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ኮሚቴ ጠቅላላ ጉባኤ ጥንቅር፣

የኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ኮሚቴ ጠቅላላ ጉባኤ አባላት ማካተት ይኖርበታል፡፡

1. ኢትዮጵያዊ/ትወልደ ኢትዮጵያዊ/ የሆነ የኢንተርናሽናል ኦሎምፒክ ኮሚቴ አባል የሆነ፣
2. በኢንተርናሽናል ስፖርት ማህበራት የተመዘገቡ እና ስፖርቶቻቸው በኦሎምፒክ፣ ፕሮግራም ወስጥ የተካተቱ አገር አቀፍ የስፖርት ማህበራት ፕሬዚዳንቶች፣
3. በኢንተርናሽናል ስፖርት ማህበራት የተመዘገቡና የታወቁ ስፖርቶቻቸው በኦሎምፒክ፣ ፕሮግራም ወስጥ የተካተቱ አገር አቀፍ የስፖርት ማህበራት ፕሬዚዳንቶች፣
4. የክልል/ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ኃላፊ/ተወካይ/፣
5. ኢትዮጵያዊ/ትወልደ ኢትዮጵያዊ/ የሆነ የአፍሪካ ኦሎምፒክ ኮሚቴ ማህበር /ANOCA/ አባል የሆነ፣
6. የኦሎምፒክ ኮሚቴው ፕሬዚዳንትና ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት፣

7. በኦሎምፒክ ተሳትፈው ሜዳሊያ ያገኙና ወድድር ያቆሙ አትሌቶች ወድድር ካቆሙበት ጊዜ ጀምሮ ለአንድ ኦሎምፒያድ ብቻ አንድ ወንድና አንድ ሴት በአባልነት ይሳተፋሉ፣

8. በኦሎምፒክ ተሳትፈው ሜዳልያ ያገኙና በወድድር ላይ ያሉ አንድ ወንድ እና አንድ ሴት አትሌቶች በማህበራቸው የሚወክሉ፣

9. ስድስቱ ታዋቂ የስፖርት ድርጅቶች ተወካዮች/ያለድምጽ/፣

10. የኢትዮጵያ ፓራሊምፒክ ኮሚቴ ፕሬዚዳንት /ያለድምጽ/፣

11. የኢትዮጵያ ጠፍ ስፖርት ማህበር ፕሬዚዳንት /ያለድምጽ/፣

12. የኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ኮሚቴ ኮሚሽኖች አንድ ተወካይ/ያለድምጽ/፣

13. በኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ኮሚቴ ጠቅላላ ጉባኤ የተመረጡ የክብር አባላት /ያለድምጽ/'

14. የኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ኮሚቴ ዋና ፀሐፊ/ያለድምጽ/፣

15. በኢንተርናሽናል ስፖርት ማህበራት የተመዘገቡና ስፖርቶቻቸው በኦሊምፒክ ኘሮግራም ወስጥ የተካተቱ ብሔራዊ የስፖርት ማህበራት ጽ/ቤት ኃላፊዎች /ያለድምጽ/፣

16. የኢትዮጵያ ዩንቨርስቲዎች ስፖርት ማህበር ፕሬዝዳንት /ያለድምጽ/፣

17. የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር አንድ ተወካይ /ያለድምጽ/፣

## 18 <u>የኢትዮጵያ ፓራሊምፒክ ኮሚቴ ጠቅላላ ጉባኤ ጥንቅር</u>

የኢትዮጵያ ፓራሊምፒክ ኮሚቴ ጠቅላላ ጉባኤ የሚከተሉትን በአባልነት ማካተት ይኖርበታል::

**1.** ኢትዮጵያዊ/ትወልደ ኢትዮጵያዊ/ የሆነ የኢንተርናሽናል ፓራሊምፒክ ኮሚቴ አባል የሆነ፣

**2.** በኢትዮጵያ ፓራሊምፒክ ኮሚቴ ፕሬዚዳንትና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት፣

**3.** በኢትዮጵያ ፓራሊምፒክ ኮሚቴ ተመዝግበው ዕወቅና ያገኙ በስፖርት ዓይነት ወይም በጉዳት ዓይነት የተቋቋሙ ብሄራዊ ፌዴሬሽኖች ኘሬዝዳንቶች፣

**4.** የክልል ወይም የከተማ አስተዳደር የፓራሊምፒክ ስፖርቶች ኘሬዚዳንቶች፣

**5.** የኢትዮጵያ ማስማት የተሳናቸው ስፖርቶች ማህበር /ያለድምጽ/፣

**6.** አካል ጉዳተኛወን በስፖርታቸው አካተው እየሰሩ ያሉ ሀገር ዓቀፍ የስፖርት ማህበራት ፕሬዝዳንቶች /ያለ ድምጽ/፣

**7.** የክልል/ከተማ አስተደደር የፓራሊምፒክ ጽ/ቤት ኃላፊ ወይም የቴክኒክ አስተባባሪ /ያለድምጽ/፣

**8.** የኢትዮጵያ ዩንቨርስቲዎች ስፖርት ማህበር ፕሬዝዳንት/ያለ ድምጽ/፣

**9.** በጠቅላላ ጉባኤ የተመረጠ ኦዲተር /ያለ ድምጽ/፣

**10.** በጠቅላላ ጉባኤ የተመረጡ ለስፖርቱ አስተዋጽኦ ያደረጉ ወይም በስፖርቱ የተለያየ አመራር በመስጠት ያገለገሉ የክብር አባላት /ያለ ድምጽ/፣

**11.** የፓራሊምፒክ ኮሚቴ ጽ/ቤት ኃላፊ /ያለ ድምጽ/፣

12. የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር ተወካይ /ያለ ድምጽ/፣

## 19. የኢትዮጵያ ማስማት የተሳናቸዉ ስፖርቶች ማህበር ጠቅላላ ጉባኤ ጥንቅር

የኢትዮጵያ ማስማት የተሳናቸዉ ስፖርቶች ፌዴሬሽን ጠቅላላ ጉባኤ የሚከተሉትን በአባልነት ማካተት ይኖርበታል::

1. ኢትዮጵያዊ/ትወልደ ኢትዮጵያዊ/ የሆነ የዓለም አቀፍ ማስማት የተሳናቸዉ ስፖርቶች ኮሚቴ አባል የሆነ፤
2. ስፖርቶቻቸው በማስማት የተሳናቸው ስፖርቶች ፕሮግራም ወስጥ የተካተቱ የአገር አቀፍ ፌዴሬሽኖች ፕሬዝዳንቶች፣
3. የክልል ወይም ከተማ አስተደደር ማስማት የተሳናቸዉ ስፖርቶች ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንቶች፣
4. የክልል /ከተማ አስተደደር ማስማት የተሳናቸዉ ስፖርቶች ፌዴሬሽን ጽ/ቤት ኃላፊዎች ወይም የቴክኒክ አስተባባሪ /ያለድምጽ/፣
5. የኢትዮጵያ ማስማት የተሳናቸዉ ስፖርቶች ፌዴሬሽን ፐሬዚዳንትና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት፣
6. በጠቅላላ ጉባኤ የተመረጠ ኦዲተር /ያለድምጽ/፣
7. በጠቅላላ ጉባኤ የተመረጡ ለስፖርቱ አስተዋጽኦ ያደረጉ ወይም በስፖርቱ የተለያየ አመራር በማስጠት ያገለገሉ የክብር አባላት /ያለድምጽ/፣
8. የኢትዮጵያ ዩንቨርስቲዎች ስፖርት ማህበር ፐሬዝዳንት/ያለድምጽ/፣
9. የኢትዮጵያ ማስማት የተሳናቸዉ ስፖርቶች ፌዴሬሽን ጽ/ቤት ኃላፊ /ያለድምጽ/፣
10. የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር ተወካይ /ያለድምጽ/፣

## 20. የኢትዮጵያ ዩንቨርስቲዎች ስፖርት ማህበር ጠቅላላ ጉባኤ ጥንቅር

የኢትዮጵያ ዩንቨርስቲዎች ስፖርት ማህበር ጠቅላላ ጉባኤ የሚከተሉትን አባላት ማካተት ይኖርበታል::

1. የኢትየጵያ ዩንቨርስቲዎች ስፖርት ማህበር አባል የሆኑ ዩንቨርስቲዎች፣
2. የአገር አቀፍ ዩንቨርስቲዎች ስፖርት ማህበር ፐሬዚዳንትና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት፣
3. የትምህርት ሚኒስቴር የስፖርት ክፍል ኃላፊ፣
4. የኢትየጵያ ዩንቨርስቲዎች የተማሪዎች ህብረት አንድ ወንድና አንድ ሴት፣
5. በጠቅላላ ጉባኤ የተመረጡ የክብር አባላት/ያለድምጽ/፣
6. የኢትየጵያ ኦሎምፒክ ኮሚቴ ተወካይ/ያለድምጽ/፣

7. የኢትዮጵያ ፓራሊምፒክ ኮሚቴ ተወካይ/ያለድምጽ/፣

8. የኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸው ስፖርቶች ፌደሬሽን ተወካይ/ያለድምጽ/፣

9. የኢትዮጵያ ዩንቨርስቲዎች ወድድር የሚያካሂደባቸው የስፖርት ማህበራት የጽ/ ቤት ኃላፊዎች /ያለድምጽ/፣

10. የጽ/ቤት ኃላፊ/ያለድምጽ/፣

11. የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር ተወካይ /ያለድምጽ/፣

## 21. የኢትዮጵያ ጠና ስፖርት ማህበር ጠቅላላ ጉባኤ ጥንቅር

የኢትዮጵያ ጠና ስፖርት ማህበር የጠቅላላ ጉባኤ የሚከተሉትን ማካተት ይኖርበታል፡፡

1. የየክልል /ከተማ አስተዳደር የጠና ስፖርት ማህበራት ፕሬዚዳንቶች፣
2. የሀገር አቀፍ የጠና ስፖርት ማህበር ፕሬዚዳንትና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት፣
3. በጠቅላላ ጉባኤ የተመረጡ የክብር አባላት/ያለድምጽ/፣
4. በጠቅላላ ጉባኤ የተመረጠ ኦዲተር/ያለድምጽ/፣
5. የማህበሩ ጽ/ቤት ኃላፊ/ያለድምጽ/፣
6. የሀገር አቀፍ የጠና ስፖርት ማህበር ወድድር የሚያካሂደባቸው ስፖርት ማህበራት ጽ/ቤት ኃላፊዎች /ያለድምጽ/፣
7. የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር ተወካይ /ያለድምጽ/፣

## 22. የስፖርት አሶሴሽኞች ጠቅላላ ጉባኤ ጥንቅር

የስፖርት አሶሴሽን ጠቅላላ ጉባኤ የሚከተሉትን ማካተት ይኖርበታል፡፡

1. በክልሎች/ከተማ አስተዳዳር ያሉ የስፖርት አሶሴሽኞች ፕሬዚዳንቶች/ ተወካዮች/፣
2. የአሶሴሽኑ ፕሬዚዳንትና የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት፣
3. የአገር አቀፍ ስፖርት አሶሴሽን በባለቤትነት የሚያወዳድራቸው ክለቦች ፕሬዚዳንቶች/ተወካዮች፣
4. የአገር አቀፍ አሶሴሽኖች በባለቤትነት የሚያወዳድራቸው ክለቦች ወስጥ ክለብ የሌላቸው ክልሎች ካሉአቸው ክለቦች አንድ ተወካይ፣
5. በአገር አቀፍ ደረጃ የተቋቋሙ የዳኞች፣ አሰልጣኞችና የተጫዋቾች ማህበራት ፕሬዚዳንቶች፣
6. በጠቅላላ ጉባኤ የተመረጡ የክብር አባላት/ያለድምጽ/፣
7. በጠቅላላ ጉባኤ የተመረጠ ኦዲተር/ያለድምጽ/፣
8. የአሶሴሽኑ ጽ/ቤት ኃላፊ/ያለድምጽ/፣
9. የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር ተወካይ /ያለድምጽ/፣

## 23. የስፖርት ማህበራት ጠቅላላ ጉባኤ ስልጣንና ተግባር

በዚህ መመሪያ ወስጥ ለእያንዳንዱ ስፖርት ማህበር የተሰጠው ስልጣን እና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ ጠቅላላ ጉባኤው፡፡

1. የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ስልጣንና ኃላፊነት የመወሰን፣

2. የሌሎች ንዑሳን ኮሚቴዎች ስልጣንና ኃላፊነት የመወሰን፣

3. የስፖርት ማህበሩን የጽ/ቤት ኃላፊ ስልጣንና ኃላፊነት የመወሰን፣

4. ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ጠቅላላ ጉባኤው የሚከተሉት ዋና ዋና ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡፡

ሀ. የስፖርት ማህበሩን ዓመታዊ የሥራ እቅድ፣በጀት እና አፈጻጸም ሪፖርት መርምሮ የሚፀድቅ፣

ለ. ደንቦችና መመሪያዎችን ማፅደቅና ተግባራዊነታቸውን ሚረጋገጥ፣

ሐ. ስትራቴጂያዊ ዕቅድ መርምሮ ማፅደቅ፣

መ. የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላትን የመምረጥ፣

ሠ. የስፖርት ማህበሩን ዓመታዊ የኦዲት ሪፖርት መርምሮ የሚፀድቅ፣

ረ. በስፖርት ማህበሩ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የተላለፉ የቅጣት ወሳኔዎችን በመመርመር የሚፀድቅና ምህረት የማስጠት

ሰ. የጠ/ጉባዔ የክብር አባላትን ማሰየም፤

## 24. የስፖርት ፌዴሬሽን ስልጣንና ተግባር

በዚህ መመሪያ አንቀፅ 23 ላይ የተጠቀሱትን ስልጣንና እና ተግባር እንደተጠበቁ ሆኖ ፌዴሬሽኖች የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሯቸዋል፡፡

1. ለመንግስት ስፖርት ፖሊሲ፣ ህግ፣ ደንብና መመሪያዎች ተገዢ መሆን፣

2. ደረጃቸውን የጠበቁ የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎችን ማንባትና ማስፋፋት እንዲሁም ከመንግስት ጋር በቅንጅት መሥራት፣

3. ስፖርቱን የሚያካከቱ የተለያዩ ሚጂያዎችን የማሰባሰብ፣የሚደራጀት፣የመተንተንና የማሠራጨት፣

4. የአገር አቀፍና ኢንተርናሽናል ወድድሮችን የማካሄድ፣

5. የስፖርት ክለቦች እንዲደራጁ መመሪያ የማውጣትና ፈቃድ የማስጠት

6. ልዩ ተሰጥኦ ያላቸውን ታዳጊ ወጣቶች በመሚልሚል ስልጠና የሚያገኙበት ሁኔታ የማመቻቸት፣

7. የሙያ ማህበራት እንዲደራጁ ድጋፍ የማስጠት፣

8. ከሚዲያ አካላት ጋር በመሥራት ስፖርቱን ለህብረተሰቡ ተደራሽ የሚድረግ፣

9. ራስን ለመቻል ገቢ የማመንጨት፣

10. የዳኞችና የአሰልጣኞችን የመሚልሚያ ማሰፈርትና ደረጃ በማውጣት ፈቃድ የማስጠት፣

11. ከዓለም አቀፍና ከአገር ውስጥ ተቋማት ጋር በመተባበር ኮርሶችን ፣ሴሚናሮችን፣ ወርክሾፖችንና ሥልጠናዎችን ማዘጋጀትና ሥራ ላይ የማዋል፣

12. ስፖርቱን በሚመለከት በአህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ስብሰባዎች መሳተፍና ወሳኔዎችን ተግባራዊ የሚድረግ፣

13. የአሰልጣኞችን እና የዳኞችን የሙሉስልጠኛ ማንዋል በተለያየ ደረጃ የማዘጋጀት፣

14. የሚሟሙወን ስፖርት በሚመለከት በሚቀርቡ ማናቸውም ክሶችና አቤቱታዎች ላይ ወሳኔ የመስጠት፣

15. አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር በክልል/ከተማ አስተዳደር ሆነ በፌዴራል ደረጃ ስፖርቱ እንዲስፋፋና እንዲያድግ ድጋፍ የሚድረግ፣

16. አመታዊ ዕቅድና የአፈጻጸም ሪፖርት ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የማቅረብ፣

17. የውስጥ መተዳደሪያ ደንብና መመሪያ በማዘጋጀት በጠቅላላ ጉባኤ የሚፀድቅ እና ተግባረዊ የሚድረግ፣

18. በዓለም አቀፍ ደረጃ የፀደቀውን እና ኢትዮጵያ የተቀበለችውን የፀረ-ዶፒንግ ኮንቬንሽን መሰረት በሚድረግ የወጡ ህጎች የማክበርና የማስከበር፣

19. ፌዴሬሽኑ በሚሟሙው ስፖርት በኢንተርናሽናልና በአገር አቀፍ ደረጃ በሚደረጉ ወድድሮችና ስልጠናዎች ለሚሳተፉ አካላት ፈቃድ የመስጠት፣

20. ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ የማህበሩን ጠቅላላ ጉባኤ ማካሄድ፣

21. ፌዴሬሽኑ የሚሟሙወን ስፖርት በተመለከተ ለተጨዋቾቸ ዝወወር እወቅና የመስጠት፣

22. ለብሔራዊ ቡድን ስፖርተኞች፣ቡድን መሪዎች እና አሰልጣኞች የህይወት እና የአካል ደህንነት ዋስትና /ኢንሹራንስ/ የመግባት፣

23. ከአፈፃፀሪ ወጣዩችና ስፖርት ሚኒስቴር የተሰጣቸውን የፈቃድ የምስክር ወረቀቶች በየአራት ዓመቱ የማደስ፣

24. የረዥም ፣የመካከለኛና የአጭር ጊዜ ዕቅድ አዘጋጅተወና በጠቅላላ ጉባዔ አፀድቀው ተግባራዊ የሚድረግ፣

25. የአሰልጣኞች፣የዳኞች፣ የአትሌቶች ማህበራት፣ ማናጀሮች እና ኤጀንት ተወካዮች መዝግቦ የመያዝ፣

26. ከስፖርት አካዳሚ እና ከስልጠና ማዕከላት ጋር ግንኙነት በመፍጠር ዘመናዊ ስልጠና እንዲሰጥ የሚድረግ፣

27. ስፖርታዊ ጨዋነት እንዲሰፍን በስፖርታዊ መርሆዎችና ሥነምግባር ዙሪያ ሥልጠና መስጠት፣ስፖርታዊ ጨዋነት ሲጣስ እርምጃ መወሰድ፣

28. ዓለም አቀፋዊ አገራዊ መመሪያ መሠረት በሚድረግ የማህበሩን የሥነምግባር የምርጫ ኮድ ያወጣል፡፡

## 25. የኢትዮጵያ የኦሎምፒክ ኮሚቴ ስልጣንና ተግባር

የኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ኮሚቴ ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል::

1. የአገሪቱን ስፖርት ፖሊሲ፣ሕጎች፣ደንቦችንና መመሪያዎችን ተግባራዊ የሚደረግ፣
2. በአገሪቱ የስፖርት ማሰልጠኛ ማዕከልና የማዘውተሪያ ስፍራዎች እንዲስፋፉ ድጋፍ ያደርጋል፣
3. የአገሪቱን ስፖርት ለማሳደግ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የመተባበር ፣
4. የኦሎምፒክ ፍልስፍናንና እንቅስቃሴን በሀገር ወስጥ ማስፋፋትና ማጠናከር፣
5. ስፖርተኞች በኦሎምፒክ ጨዋታዎች እንዲካፈሉ ሚደረግና በኢንተርናሽናል ኦሎምፒክ ኮሚቴ ድጋፍ በሚሰጣቸው አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ጨዋታዎች ሀገራችን ተሳታፊ እንድትሆን ድጋፍ የማጠት፣
6. የኦሎምፒክ መሠረታዊ ፅንሰ ሀሳቦች በየደረጃው ባሉ የስፖርት ማህበራት ከስፖርት ሳይንስ ትምህርት ጋር ተቀናጅተው እንዲሰጡ የሚደረግ፣ የሚደረግ፣
7. በስፖርት ስልጠና፣ምርምርና፣ወድድሮች ረገድ ድጋፍ የሚደረግ፣
8. የሥራ እንቅስቃሴዉን ሪፖርት ቢጊዜው ለዓለም አቀፍ ኦሎምፒክ ኮሚቴ ሪፖርት የማቅረብ፣
9. የኢንተርናሽናል ኦሎምፒክ ኮሚቴ ቻርተርንና ሌሎች ደንቦች በሀገር ወስጥ ማክበር እና ማስከበር፣
10. የስፖርት ትጥቅና መሣሪያዎች ለተለያዩ አጋር አካላት ህግና ስርዓት ማስረት በሚደረግ ድጋፍ ያደርጋል፣
11. የስፖርት ለሁሉም እንዲስፋፋና እንዲያድግ ማበረታታትና ድጋፍ የማጠት፣
12. ወጤታማና ምርጥ አትሌቶችን የሚፍራት ስራ እንዲጠናከር ማበረታቻና ድጋፍ የማጠት፣
13. በዓለም አቀፍ ደረጃ የፀደቀወን እና ኢትዮጵያ የተቀበለችወን የፀረ-ዶፒንግ ኮንቬንሽን ማስረት በሚደረግ የወጡ ህጎችን የማክበር የማስከበር ተባብሮ የማስራት፣
14. የአገር አቀፍ የስፖርት ተቋማትንና በአገራችን ተከፈቱ ዓለም አቀፍ የስፖርት ተቋማትን አቅም የማጎልበትና የመደገፍ፣
15. ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ጠቅላላ ጉባኤ የማካሄድ፣
16. በክልሎች /ከተማ አስተዳደሮች ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በማካፈት የስፖርቱን ማስፋፋት የማጠናከር፣
17. የስፖርት ልማቱን ሊደግፉ የሚችሉ ገቢ የሚመነጩ ስራዎችን የማከናወን፣
18. ዓመታዊ ዕቅድና የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ለሚኒስቴሩ ማቅረብ፣
19. ሌሎች ዓላማውን ለማስፈጸም የሚዱ ተግባራትን ማከናወንን ያጠቃልላል፡፡

## 26. የኢትዮጵያ ፓራሊምፒክ ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባር

የኢትዮጵያ የፓራሊምፒክ ኮሜቴ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

1. የአገሪቱን ስፖርት ፖሊሲ፣ሕጎች፣ደንቦችንና መመሪያዎችን ተግባራዊ ማድረግ፣
2. የፓራሊምፒክ ስፖርታዊ እንቅስቃሴን በአገር ወስጥ የማስፋፋትና የማሳደግ፣
3. በኢንተርናሽናልና በአገር አቀፍ ደረጃ በሚዘጋጀው የፓራሊምፒክ ስፖርት ጨዋታዎች የአካል ጉዳተኛወን ሕብረተሰብ ተሳትፎ በማሳደግ አገራችንን ተጠቃሚ የማድረግ፣
4. የፓራሊምፒክ ስፖርቶች በመላሀገሪቱ ስለሚስፋፋበትና ስለሚዳደግበት ሁኔታ ስልጠና ማስጠትና ምርምር እንዲደረግ ምቹ ሁኔታ የመፍጠር፣
5. የፓራሊምፒክ መሠረታዊ ፅንሰ ሃሳቦች በየደረጃው በሚገኑ የትምህርት ተቋማት በሚሰጥ የስፖርት ሳይንስ ትምህርት ወስጥ ለማካተት የሚያስችል ሰልት የመቀየስ፣
6. የኢንተርናሽናል ፓራሊምፒክ ኮሜቴ ቻርተርና ሌሎች ደንቦችን አክብሮ የማንቀሳቀስ፣
7. ስፖርቱን የሚመለከቱ መረጃዎችን የማሰባሰብ፣የማደራጀት፣የመተንተንና የማሰራጨት፣
8. ስፖርታዊ ጨዋነት እንዲሰፍን በስፖርታዊ መርሆዎችና ሥነ ምግባር ዙሪያ ሥልጠና ማስጠት፣ስፖርታዊ ጨዋነት ሲጣስ እርምጃ መወሰድ፣
9. የክልልና ከተማ አስተዳደር የፓራሊምፒክ ስፖርቶችን አቅም የማጎልባትና የመደገፍ፣
10. የብቃት ደረጃ ያላቸው የፓራሊምፒክ ስፖርቶችን ለማፍራት የሚያስችል ዘመናዊ የስልጠና ስልት የመቀየስና ተግባራዊ የማድረግ፣
11. ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ የማህበሩን ጠቅላላ ጉባኤ የማካሄድ፣
12. ለፓራሊምፒክ ስፖርታዊ እንቅስቃሴ ምቹ የሆኑ የማዘወተሪያ ሥፍራዎችና ማቴሪያሎችን እንዲሟሉ ጥረት የማድረግ፣
13. ዓመታዊ ዕቅድ የአፈጻጸም ሪፖርት ለሚኒስቴሩ ማቅረብ፣
14. ኢትዮጵያ የተቀበለችወን የፀረ-ዶፒንግ ኮንቬንሽንና የወጡ ሕጎች፤የማክበርና የማስከበር፣
15. በየስፖርት ዓይነቱ ፌዴሬሽኖችን መደገፍ እና ወድድሮችን ራሳቸው እንዲመሩ የማስቻል፣
16. ሌሎች ዓላማወን ለማስፈጸም የሚረዱ ተግባራትን የማከናወን ያጠቃልላል፡፡

## 27 የኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸዉ ስፖርቶች ፌደሬሽን ስልጣንና ተግባር

የኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸዉ ስፖርቶች ማህበር የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

1. የአገሪቱን ስፖርት ፖሊሲ፣ሕጎች፣ደንቦችንና መመሪያዎችን ተግባራዊ ማድረግ፣
2. መስማት የተሳናቸው የህብረተሰብ ክፍሎቸ በስፖርታዊ እንቅስቃሴ ላይ ያላቸወን ተሳትፎ በአገር ወስጥ የማስፋፋትና የማሳደግ፣

3. በኢንተርናሽናል በአገር አቀፍ ደረጃ በሚዘጋጀው ማስማት የተሳናቸዉ ስፖርቶች ጨዋታዎች ማስማት የተሳናቸዉ ሕበረተሰብ ክፍል ተሳትፎ ባማእደግ አገራችንን ተጠቃሚ የማድረግ፣
4. ማስማት የተሳናቸዉ የህብረተሰብ ክፍሎች በስፖርታዊ እንቅስቃሴ እንዲሳተፉ በመላ ሀገሪቱ ስልጠና ማስጠትና ምርምር እንዲደረግ ምቹ ሁኔታ የመፍጠር፣
5. ዓለም አቀፍ ማስማት የተሳናቸዉ ስፖርቶች ኮሚቴ መሠረታዊ ፅንስ ሃሳቦች በየደረጃው በሚገኙ የትምህርት ተቋማት በሚሰጥ የስፖርት ትምህርት ወስጥ ለማካተት የሚያስቸል ስልት የመቀየስ
6. የዓለም አቀፍ ማስማት የተሳናቸዉ ስፖርቶች ኮሚቴ ቻርተርና ሌሎች ደንቦችን አክብሮ የማንቀሳቀስ፣
7. ስፖርትን የሚመለከቱ መረጃዎችን የማሰባሰብ፣የማደራጀት፣የመተንተንና የማሰራጨት፣
8. ስፖርታዊ ጨዋነት እንዲሰፍን በስፖርታዊ መርሆዎችና ሥነ ምግባር ዙሪያ ሥልጠና ማስጠት፣ስፖርታዊ ጨዋነት ሲጣስ እርምጃ መወሰድ፣
9. የክልልና የከተማ አስተዳደር ማስማት የተሳናቸዉ ስፖርቶች ማህበር አቅም የማጎልበትና የመደገፍ፣
10. ምርጥ ስፖርተኞችን ለማፍራት የሚያስችል ዘመናዊ የሥልጠና ስልት የመቀየስና ተግባራዊ የማድረግ፣
11. ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ የማህበሩን ጠቅላላ ጉባኤ የማካሄድ፣
12. ለስፖርታዊ እንቅስቃሴ ምቹ የሆኑ የማዘውተሪያ ሥፍራዎችና ማቴሪያሎችን እንዲሟሉ ጥረት የማድረግ፣
13. ዓመታዊ ዕቅድ የአፈጻጸም ሪፖርት ለሚኒስቴሩ ማቅረብ፣
14. ኢትዮጵያ የተቀበለችውን የፀረ-ዶፒንግ ኮንቬንሽንና የወጡ ሕጎች፤የማክበርና የማስከበር፣
15. ሌሎች ዓላማውን ለማስፈጸም የሚረዱ ተግባራትን የማከናወን ያጠቃልላል፡፡

28.<u>የኢትዮጵያ ዩንቨርስቲዎች ስፖርት ማህበር ሥልጣንና ተግባር</u>

የኢትዮጵያ ዩንቨርስቲዎች ስፖርት ማህበር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

1. የአገሪቱን ስፖርት ፖሊሲ፣ሕጎች፣ደንቦችንና መመሪያዎችን ተግባራዊ ማድረግ፣
2. በዩንቨርስቲዎች የስፖርትን ለማስፋፋትና ለማእደግ የሚያስችል ስልት ይቀይሳል፣ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣
3. በዩንቨርስቲዎች የስፖርት ፌስቲቫል የወድድር ደንብ በስራ ላይ እንዲወል ያደርጋል፣
4. በሀገር ወስጥ የዩንቨርስቲዎች የስፖርት ወድድሮችንና ፌስቲቫሎችን ያዘጋጃል፣

5. የዩንቨርስቲዎች የስፖርት ማህበር መተዳደሪያ ደንብ ያዘጋጃል፣እንደ አስፈላጊነቱ ያሻሽላል፣ተግባረዊም ያደርጋል፣
6. የዩንቨርስቲዎች ስፖርት አደረጃጀትና አሠራር በየስፖርቱ ያለውን ዓለም አቀፍ ሕግና ደንብና የተከተለና ስፖርታዊ ጨዋነት የተላበሰ እንዲሆን ያደርጋል፣
7. በስፖርቱ ዘርፍ ልዩ ልዩ ትምህርቶችን፣ሴሚናሮች፣ፌስቲቫሎች፣ወርክሾፖችንና ስልጠናዎችን ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ከሀገር ወስጥና ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ያዘጋጃል ፣
8. ከአህጉር አለም አቀፍ ዩንቨርስቲ ተማሪዎች የስፖርት ማህበርና አቻ ማህበራት ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንዲኖር ጥረት ያደርጋል፣
9. ስለ ዩንቨርስቲዎች ስፖርት ዕድገት የአጭር፣የመካከለኛ እና የረዥም ጊዜ ዕቅድና ፕሮግራም አወጥቶ በሥራ ላይ እንዲወል ያደርጋል፣
10. የዩንቨርስቲዎች ስፖርት ወድድር ዝግጅትና አመራርን ሕጋዊ ለሆነ አካል በወል ስምምነት ሰጥቶ እንዲካሄድ ያደርጋል፣
11. ከሚመለከታቸው አገር አቀፍ ስፖርት ተቋማት፣መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር አስፈላጊውን ግንኙነት ያደርጋል፣
12. ኢትዮጵያ የተቀበለችውን የፀረ-ዶፒንግ ኮንቬንሽን መሠረት የወጡ ሕጎች፤የማክበርና የማስከበር፣
13. ዓመታዊ ዕቅድና የሥራ የአፈጻጸም ሪፖርት ሚመለከተው አካልያ ያቀርባል፣
14. በአህጉርና በዓለም አቀፍ ዩንቨርስቲዎች ስፖርት ወድድሮች፣ ፌስቲቫሎች፣ ስብሰባዎችና ወርክሾፖች ላይ ይካፈላል::
**15**. ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ የማህበሩን ጠቅላላ ጉባኤ ያካሄዳል፣
16. ወጤታማ አገርን ሊያስጠሩ የሚያስችሉ ምርጥ ስፖርተኞች እንዲፈሩ ጥረት ያደርጋል፣
17. ስፖርታዊ ጨዋነት እንዲሰፍን በስፖርታዊ ሞርሆዎችና ሥነ ምግባር ዙሪያ ሥልጠና ማስጠት፣ስፖርታዊ ጨዋነት ሲጣስ እርምጃ መወሰድ፣
18. ሌሎች ዓላማውን ለማስፈጸም የሚረዱ ተግባራትን የማከናወን::

## 29. <u>የኢትዮጵያ ጠና ስፖርት ማህበር ተግባርና ኃላፊነት</u>

1. የአገሪቱን ስፖርት ፖሊሲ፣ሕጎች፣ደንቦችንና መመሪያዎችን ተግባራዊ ሚድረግ፣
2. የጠና ስፖርትን ለማስፋፋትና ለማእደግ የሚያስችል ስልት ይቀየሳል ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣
3. በየክልልና ከተማ አስተዳዳር የተቋቋሙ የጠና ስፖርት ማህበራትን ይደግፋል፣
4. አገር አቀፍ የጠና የስፖርት ወድድሮችንና ፌስቲቫሎችን ያዘጋጃል፣በበላይነት ይመራል፣አፈጻጸማቸውንም ይከታተላል፣

5. በጠፍ ስፖርት ዙሪያ ትምህርቶችን፣ሲሚናሮች፣ፌስቲቫሎች፣ወርክሾፖችንና ስልጠናዎችን ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ከአገር ወስጥና ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ያዘጋጃል፣
6. ከአህጉር እና አለም አቀፍ የጠፍ ስፖርት ማህበርና አቻ ማህበራት ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንዲኖር ጥረት ያደርጋል፣
7. ስለ ጠፍ ስፖርት ዕድገት የአጭር፣የመካከለኛና የረዥም ጊዜ ዕቅድና ፕሮግራም አወጥቶ በሥራ ላይ እንዲወል ያደርጋል፣
8. የጠፍ ስፖርት ወድድር ዝግጅትና አሜራርን ሕጋዊ ለሆነ አካል በወል ስምምነት ሰጥቶ እንዲካሄድ ያደርጋል፣
9. ከሚመለከታቸው አገር አቀፍ ስፖርት ማህበራት፣መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር አስፈላጊወን ግንኙነት ያደርጋል፣
10. ኢትዮጵያ የተቀበለችወን የፀረ-ዶፒንግ ኮንቬንሽን ማስረት በማድረግ የወጡ ሕጎች፤የሚከበርና የሚከበር፣
11. ዓመታዊ ዕቅድና የሥራ የአፈጻጸም ሪፖርት ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፣
12. በአህጉርና በዓለም አቀፍ የጠፍ ስፖርት ወድድሮች፣ፌስቲቫሎች፣ስብሰባዎችና ወርክሾፖች ላይ ይካፈላል ::
**13.** ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ የማህበሩን ጠቅላላ ጉባኤ ያካሄዳል፣
14. በጠፍ ስፖርት ዙሪያ ትምህርትና ስልጠና እንዲሰጥ ያደርጋል፣
15. አጠቃላይ የማህበሩ እንቀስቃሴ ለሚመለከታቸው አካላት ሪፖርት ያደርጋል፣
16. ሌሎች ዓላማወን ለማስፈጸም የሚረዱ ተግባራትን የሚከናወን፡፡

## 30.<u>የስፖርት አሶሴሽን ስልጣንና ተግባር</u>

1. የአሶሴሽኑ ስልጣንና ተግባር በአንቀጽ 23 ና 24 የተዘረዘሩትን ሥልጣንና ተግባር ያጠቃልላል፡፡
2. የስፖርት ክለቦች ስልጣንና ተግባር በፌዴሬሽኖች ወይም አሶሴሽኖች ጠቅላላ ጉባኤ በሚፀድቅ የመተዳዳሪያ ደንብ የሚወሰን ይሆናል፡፡

## 31 <u>የስፖርት ማህበራት ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ጥንቅር</u>

የስፖርት ማህበራት ከ7-11 የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት የሚኖራቸዉ ሆኖ፤ -

1. ፕሬዝዳንት፣
2. ተቀዳሚ ምክትል ፕሬዝዳንት/ እንደ አስፈላጊነቱ/

3. ም/ፕሬዝዳንት፣
4. ዓቃቢ ንዋይ፣
5. አባላት 4-8፣
6. የሥፖርት ማህበሩ የጽ/ቤት ኃላፊ፣
7. በተለይም ለኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ኮሜቴ በቻርተሩ መሠረት ዋና ፀሐፊ የሚሾረው ሆኖ እያንዳንዱ የስፖርት ማህበር 30 % ሴቶችን ሥራ አስፈጻሚ ኮሜቴ አባልነት ማከተት ይኖርበታል፡፡

## 32. የስፖርት ማህበራት የሥራ አስፈፃሚ ሆኖ ለመሚጥ የሚየበቃ መመዝኛዎች

የስፖርት ማህበራት የሥራ አስፈጻሚ ኮሜቴ አባል ሆኖ ለመሚጥ የሚከተሉትን መመዝኛዎች ማሟአት ያስፈልጋል፡፡

1. ኢትዮጵያዊ/ ትወልደ ኢትዮጵያዊ / የሆነ
2. ጥሩ ስነ ምግባር ያለው፣
3. መበቱ በሕግ ያልተገፈፈ፣
4. የእዕምሮ ህመምተኛ ያልሆነ፣
5. በብልሹ አሠራር ወንጀል ተከሶ ያልተፈረደበት፣
6 ቢቻል በኢንተርናሽናል ቋንቋ መግባባት የሚቹል፣
7 ከላይ ከ1-6 የተጠቀሱት እንደተጠበቁ ሆኖ ማህበራቱ ዝርዝር መመዝኛዎችን ያወጣሉ፡፡

## 33. የሥራ አስፈጻሚ ኮሜቴ አባላት የምርጫ አፈፃፀም ሂደት

### I. ቅድመ ምርጫ

1. የአገር አቀፍ ስፖርት ማህበራት የሥራ አስፈጻሚ ኮሜቴ አባላት ምርጫ የሚከናወነው በማህበራቱ ጠቅላላ ጉባኤ በተሚጡ የምርጫ አስፈጻሚ ኮሜቴ አካላት አማካኝነት ይሆናል፡፡

2. የሀገር አቀፉ ስፖርት ማህበሩ ከምርጫው ቀን 2 ወር በፊት የመወዳደሪያወን ቅጽ ለተወዳዳሪ አካላት ያስረክባል፡፡
3. የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሆኖ መወዳደር የሚፈልግ ግለሰብ ቢያንስ ከአንድ ክልል/ከተማ አስተዳዳር ፌዴሬሽን እና ከአምስት ክለቦች የድጋፍ ደብዳቤ ማግኘት አለበት፣
4. የክልል/ከተማ አስተዳዳር ስፖርት ፌዴሬሽኖችና ክለቦች የጽ/ቤታቸው ማህተም ያረፈበትን ድጋፍ ደብዳቤ ትክክለኛነቱን አረጋግጠው ለእጩዎች ያስረክባሉ፣
5. ዕጩ ተወዳዳሪው ከክልል/ከተማ አስተዳዳሩ ፌዴሬሽንና ክለቦች የተረከበወን ድጋፍ ደብዳቤ ከምርጫ ከ2 ወር በፊት ለአገር አቀፉ ስፖርት ማህበር ምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴ ያስረክባል፣
6. የምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴው የቀረቡትን ዕጩዎች ዝርዝር ትክክለኛነት አረጋግጦ ከምርጫው 20 ቀን□ በፊት ይፋ ያደርጋል፣ ሆኖም አከራካሪ ጉዳዮች ካጋጠሙ በኢንተርናሽናል ስፖርት ማህበሩ ህግ ማስረት ተግባራዊ ይሆናል፣
7. የክልል/ ከተማ አስተዳደሩ ስፖርት ማህበራት ለፕሬዝዳንትነት 2 ለስራ አስፈጻሚ 3 እጩዎችን ማቅርብ ይችላል፣
8. እጩ ተወዳዳሪዎች የምርጫ ቅስቀሣ ማድረግ የሚችሉት ምርጫው 1ወር ሲቀረው ለተከታታይ 28 ቀናት ይሆናል፡፡

## II. <u>በምርጫ ወቅት</u>

1. ምርጫው ሚስጥራዊ በሆነ መንገድ ይካሄዳል፤
2. የስፖርት ማህበሩ የምርጫ አስፈጻሚ አካል የእጩዎቹን ፕሮፋይል ለጠቅላላ ጉባኤው በዝርዝር ማቅረብ አለበት፤
3. የስራ ዘመናቸውን የጨረሱ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ድምፅ ማስጠት አይችሉም፡
4. የስፖርት ማህበሩን ወይም የዓለም አቀፍ ስፖርት ማህበሩን የምርጫ ኮድ ማስረት በማድረግ በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ በጸደቀው ደንብ መሠረት ምርጫው የሚጸም ይሆናል፣
5. ለፕሬዝዳንትነት የቀረቡ እጩዎች ለብቻቸው የሚወዳደሩ ሲሆን ለፕሬዝዳንትነት ተወዳድረው ያልተመረጡ ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባለነት መወዳደር አይችሉም፡፡
6. ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባልነት ከተመረጡት መካከል ለተቀዳሚ/ለምክትል ፕሬዝዳንትነት ጠ/ጉባኤው ድምጽ ይሰጣል፤

7. ለፕሬዝዳንነትና ለሥራ አስፈጻሚ ኮሜቴ አባልነት የተመረጡ የኮሜቴ አባላት ያገኙት ድምጽ ለጠቅላላ ጉባኤው ማለጽ አለበት፡

8. የምርጫ የአስፈፃሚ ኮሜቴ በእለቱ የተመረጡ የስራ አስፈጻሚ ኮሜቴ አባላትን ለጠ/ጉባኤ ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

### III. ድህረ ምርጫ

1. በስፖርት ማህብሩ የተመረጡ የሥራ አስፈጻሚ ኮሜቴ አባላት ስም ዝርዝርና የስራ ሀላፊነት ለወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር እና በየደረጃ ማወቅ ለሚገባቸው አባላት ማሳወቅ አለበት፤
2. በቀድሞ እና በአዲስ በተመረጡ የሥራ አስፈጻሚ ኮሜቴ አባላት መካከል የርክክብ ስርዓት በአንድ ሳምንት ጊዜ ወስጥ መካናወን አለበት፡፡
3. ማህበሩ/ኮሜቴው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን አዲስ ለተመረጡ የሥራ አስፈጻሚ ኮሜቴ አባላት የስራ መመሪያ እንዲሁም የስራ ዘመናቸውን ለጨረሱ አባላት ዕውቅና በማስጠት በክብር ያሰናብታል፣

## 34. የሥራ አስፈጻሚ ኮሜቴ አባላት የሥራ ዘመን

1. አለምፒክ ኮሜቴን ጨምሮ የስፖርት ማህበራት የሥራ አስፈጻሚ ኮሜቴ አባላት የሥራ ዘመን የሚያበቃው በ4 ዓመት ይሆናል፡፡
2. የአገልግሎት ዘመናቸውን የጨረሱ የሥራ አስፈፃሚ ኮሜቴ አባላት ለ2ጊዜ ብቻ በድጋሚ ሊመረጡ ይጫላሉ ሆኖም ግን ከአንድ ምርጫ ዘመን በኃላ ሊመርጡ ይችላሉ፤
3. የስፖርት ማህበራት የሥራ አስፈጻሚ ኮሜቴ አባላት ምርጫ የሚከናወነው በአራተኛው ዓመት መጨረሻ ይሆናል፡፡
4. አንድ የሥራ አስፈጻሚ ኮሜቴ አባል ከስፖርት ማህብሩ መልቀቅ በፈልግ ለማህበሩ በጽሐፍ ማቅረብ አለበት ማህበሩም ጥያቄዉን ለጠቅላላ ጉባዔዉ በማቅረብ ጉባዔዉ ሲያፀድቀዉ ብቻ ለለቅ ይችላል፡፡
5. በለቀቁ የሥራ አስፈጻሚ ኮሜቴ አባላት ቦታ የስፖርት ማህበሩ የማሟያ ምርጫ ያካሄዳል፣በማሟያ ምርጫ የተመረጠ የስራ አስፈጻሚ ኮሜቴ የሥራ ዘመን ቀሪ የስፖርት ማህበሩ የስራ ዘመንን ይሆናል፡፡

## 35 የኢመርጀንሲ ኮሜቴ ሥልጠንና ተግባር

1. የሥራ አስፈጻሚ ኮሜቴ ወሳኔዎችን የሚጠይቁ ተግባራት ሲኖሩና ነገር ግን የሥራ አስፈጻሚ ኮሜቴ አባላት ተሟልተው በማይገኙበት ወቅት የሥራ አስፈፃሚ ኮሜቴ አባላት ቦታ በመተካት አስፈላጊ የሆኑ ወሳኔዎችን ይወስናሉ፡፡

2. ወሳኔወን በሚወስኑበትና እንዲፈጽሙ በሚዘቡበት ወቅት የተቀማጡትን ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች የማክበርና የማስከበር ኃላፊነት አለባቸው፡፡

3. ኮሚቴው ባከናወናቸው ተግባራት ሁሉ ሃላፊነትና ተጠያቂነት አለበት፣

4. በኮሚቴው የተከናወኑ ሁኛቸውም ተግባራት ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ቀርበው መፅደቅ አለባቸው፡፡

## ክፍል አራት

## ስለ ስፖርት ማህበራት ምዝገባ፣ ገቢ የማሰባሰብ፣ የውጭ ግንኙነት እና የውጭ ጉዞ

### 36.ስለ ስፖርት ማህበራት ምዝገባና ዕውቅና ማግኘት፡-

1. ከዚህ በፊት ያልተመዘገበና ዕውቅና ያላገኘ የስፖርት ማህበር በዚህ መመሪያወስጥ የተዘረዘሩትን መመዘኛዎች አሟልቶ ከተገኘ ሊመዘገብ ይችላል፣
2. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀፅ አንድ የተገለፀው ቀደም ሲል የስፖርት ማህበራት ስለሚቋቋሙበት ሁኔታ ለመወሰን (በ2003) በወጣው መመሪያ መሠረት ተደራጅተው /የምስክር ወረቀት/ የተሰጣቸው የስፖርት ማህበራት አይመለከትም፣
3. የስፖርት አሶሴሽኖች የፌዴሬሽንን ማስፈርት ሲያሟሉ የቀድሞ ስያሜቸውን ይዘው በፌዴሬሽን ደረጃ አድገው መመዝገብ ይችላሉ፡፡

### 37.በስፖርት ማህበራት ምዝገባ የክፍሎችና ከተማ /አስተዳደሮች

### ተግባርና ኃላፊነት

1. የወጣውን የስፖርት ማህብራት ማቋቋሚያ መመሪያ በሚድረግ የክልሎች / ከተማ አስተዳር/ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ወይም ስፖርቱን እንዲመሩ በሕግ ኃላፊነት የተሰጠው አካል የክልሉን ስፖርት እንቅስቃሴ ተጨባጭ ሁኔታ ከግምት ወስጥ በማስገባት የክልል ስፖርት ማህበራት ማቋቋሚያ / መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. የክልል/ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ቢሮዎች የመመሪያው ተፈፃሚነት ማካታተልና ሚደገፍ ይኖርባቸዋል ፡፡

3. በክልልና ከተማ አስተዳደር ደረጃ የተቋቋሙ የስፖርት ማህብራት ባሉበት የአስተዳደር እርከን ካለው ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ወይም ስፖርቱን እንዲመራ ኃላፊነት በተሰጠው አካል አማካይነት ተመዝግቦ ዕውቅና ማግኘት እና ለአገር አቀፍ ስፖርት ማህበር ማሳወቅ ይጠበቅባቸዋል፡፡

## 38 የስፖርት ማህበራት ገቢ ስለሚያመነጩበት ሁኔታ

1. በገቢ ማመንጫ ሥራ ላይ ለመሠማራት የስፖርት ማህበራት ዝርዝር ጥናትና ዕቅድ በማዘጋጀት ጠቅላላ ጉባኤዎቻቸው አቅርበው ማፀደቅ ይኖርባቸዋል፣
2. ለጠቅላላ ጉባኤ የሚቀርበውና የሚፀድቀው የገቢ ማመንጫ ዕቅድ ማህበራት ከተቋቋሙበት ዓላማ ጋር ተያያዥነት ያለውና የስፖርቱን ዓላማ የሚያሳካ ሊሆን ይገባል'
3. የስፖርት ማህብራት ቋሚ የገቢ ማመንጫ የስፖርት ፕሮግራሞችን ስራዎች ያዘጋጃሉ'
4. የስፖርት ማህበራት የሚያመነጩትን ገቢም ሆነ ከመንግሥት የሚሰጣቸው ድጎማ ለዓላማቸው ማስፈፀሚያ ስለማዋላቸው በየዓመቱ በውጭና በውስጥ ኦዲተሮች በማስመርመር ለጠቅላላ ጉባኤያቸው እና ለሚኒስቴሩ ሪፖርት የማድረግ ግዴታ አለባቸው፡፡

## 39. የውጭ ግንኙነት

1. የአገር አቀፍ የስፖርት ማህበራት በውጭ አገር ከሚያደርጉ ኢንተርናሽናል፣ አህጉራዊና አቻ ማህበራትና ተቋማት ጋር ግንኙነት ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡
2. ማህበራቱ የሚያደርጉት ግንኙነት የሚመሩትን ስፖርት ለማስፋፋትና መላሳደግ ገንቢ ሚና የሚጫወት ሊሆን ይገባል፡፡
3. የውጭ ግንኙነት መሠረቱ የአገራችንና ኢንተርናሽናል ህጎችና መመሪያዎችን የተከተለና ማእከል ያደረገ መሆን አለበት፡፡

## 40. የውጭ ጉዞ ዓላማ

የስፖርት ማህበራት ወደ ውጭ የሚያደርጉት ጉዞ፣

1. ለስፖርት ስልጠና እና የቴክኒክ ትብብር፣
2. ለስፖርታዊ ወድድርና ፌስትቫል፣
3. ለስፖት ማህበሩ ፕሮግራሞችን ስራዎች፣

4. ለስብሰባ እንዲሁም ለሃገር እና ለስፖርቱ የሚጠቅም ድጋፍ ልምድና ተሞክሮ ለማግኘት ለሆን ይችላል፡፡

## 41. የውጭ ጉዞን ፈቃድ አሰጣጥ

የውጭ ጉዞ ሲኖር በዚህ መመሪያ አንቀጽ 40 ከንዑስ አንቀጽ 1-4 የተዘረዘሩትን ለማካካት በሚከተለው ሁኔታ የሚዯራ ይሆናል፡፡

1. በአንቀጽ 40 ለተጠቀሱት ዓላማዎች ለሚደረጉ የወጪ ጉዞ ፈቃድ ጥያቄዎች የሚቀበው በስፖርቱ ዓይነት ለተቋቋመው አገር አቀፍ የስፖርት ማህበር ነው፡፡
2. የስፖርት ማህበሩ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት  የውጭ ጉዞውን ፈቃድ በሕጉና በደንቡ መሠረት አጣርቶና ሕጋዊ ሂደቶችን ተከትሎ ይፈቅዳል፣ ዝርዝራቸውንም ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ያሳውቃል፡፡'
3. የስፖርት ማህበሩ ፕሬዚዳንት ወይም ምክትል ፕሬዚዳንት የወጪ ጉዞ ለሚኒስትር መ/ቤቱ ቀርቦ ፈቃድ ማስጠት አለበት፣
4. ሕጋዊ አሠራሩን ያልተከተለ ወይም በሕጋዊ አሠራር ሽፋን የሚደረግ ዓላማውን የሳተ የውጭ ግንኙነትና ጉዞ  በህግ  ያስጠይቃል ፡፡
5. ከስፖርቱ ጋር የተያያዘ የውጭ ጉዞ ፈቃድ የሚሰጠው ጥሪ ለተደረገለት ወይም ጉዳዩ በቀጥታ ለሚመለከተው ሰው መሆን አለበት፣
6. አስቸኳይና ድንገተኛ የውጭ ጉዞ ፕሮግራሞች ሲያጋጥሙ በተገኘው ፈጣን የመልዕክት ዘዴ ማሳወቅ አለበት፡፡

## 42. ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ

የስፖርት ማህበራት ሃገርን ወክለው ከሄዱበት የውጭ ጉዞ ከተመለሱ በኋላ የሚከተሉትን ዝርዝር ነጥቦች ያካተተ የፅሁፍ ሪፖርት በ15 ቀናት ወስጥ ለስፖርት ማህበሩ የማቅረብ ግዴታ ይኖርባቸዋል፡፡

1. ጉዞው የፈጀው ጊዜ፣
2. ጉዞው ከተቀማጠለት ግብ አኳያ የተገኘ ወጤት ልምድና ተሞክሮ
3. ክትትል የሚጠይቁ ቀጣይ ተግባራትና ስለሚጠበቅ ድጋፍ፣
4. በጉዞው ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች እና እነሱን ለመፍታት የተደረጉ ጥረቶች፣

5. ከማህበሩ ፈቃድ አግኝተው ወደ ውጭ ጉዞ የሚያደርጉ ሌሎች የልዑካን ቡድን አባላት በአንቀጽ 40 ከተራ ቁጥር 1-4 የተጠቀሰው ሚከል በሚድረግ ፈቃድ ለሰጣቸው የስፖርት ማህበር ጽሐፍ ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ አለባቸው፡፡

## ክፍል አምስት

## □□ □□ □□□□□□□

### 43. ስለፋይናንስና ንብረት አጠቃቀም

የስፖርት ማህበራት የፋይናንስና ንብረት ምርመራን በሚመለከት የሚከተለ፤ትን ሚፈፀም ይኖርባቸዋል፡፡

1. ሁለትእና ከዚያ በላይ እንደ አስፈላጊነቱ የተቀሳቃሾችና አንድ የውጭ ምንዛሬ የባንክ አካወንቶችን መክፈትና ሂሳቡን በሦስቱ አባላት ማለትም በፕሬዚዳንቱ፣በዓቃቢ ነዋዩ/ ፋይናንስ ኃላፊ/ እና የጽ/ቤት ኃላፊ ስምና ጣምራ ፊርማ ማንቀሳቀስ ይኖርባቸዋል፣
2. ከምንግስት የሚያገኙትን ንብረት እና ፋይናንስ በመንግስት የፋይናንስ ደንብ መሠረት በወስጥ ኦዲተር የሚስመርመርና የሚስተዳር ኃላፊነት ያለባቸው ሲሆን፣ በዓመት አንድ ጊዜ የፋይናንስ አጠቃቀማቸወን ሪፖርት ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ማቅረብ ፣
3. የሥፖርት ማህበራት የራሳቸው ገቢ በማምንጩ ወይም ከሌሎች ምንጮች የሚያገኙአቸወን ፋይናንስና ንብረት ጉባኤው በሚያወጣው የፋይናንስ ደንብ መሠረት የሚስተዳደርና በወስጥ ወይም በውጭ ኦዲተር አስመርምረው ለጠቅላላ ጉባኤ የኦዲት ሪፖርት የማቅረብ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

### 44 .ስለስፖርት ማህበራት የሙያ ሥነ-ምግባር መመሪያ

በሚኒስቴሩ ተመዝግበው ዕወቅና ያገኙ የሥፖርት ማህበራት ሁሉ ተግባርና ኃላፊነታቸወን በትክክል ለመወጣት የሚያስችላቸወን የሙያ ሥነ-ምግባር የመመሪያ /Code of Ethics/ በማዘጋጀት በጠቅላላ ጉባኤያአው በሚፀደቅ በአሚራሮቻቸው፣ በስፖርት ባለሙያዎች፣ በዳኞች፣ በስፖርተኞችና በሌሎችም በስፖርቱ እንቅስቃሴ ወስጥ በሚሳተፉ አካላት ዘንድ እንዲተገበር ሚድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

### 45 የተከለከሉ ተግባራት

የስፖርት ማህበራት የሚከተሉትን ተግባራት ሚፈፀም የለባቸውም፡

1. ምንም ዓይነት ምዝገባ ሳያደርጉና የምስክር ወረቀት ሳይዙ ማንቀሳቀስ፣
2. በሃይማኖት፣በፖለቲካ፣ በጎሳና በዘር ሚደራጀት፣ በዚህ ሁኔታ የተደራጀ ክለቦችን ተቀብሎ ዕውቅና ማስጠት፣
3. የዚህንም መመሪያ ድንጋጌዎች የሚፃረሩ ተግባራትን ማከናወን፣
4. የመንግስት ፖሊሲዎችና ሕጎችን እንዲሁም ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚያወጣቸውን ስፖርት ነክ መመሪያዎችንና ሰርኩላሮችን መጣስ ወይም ተግባራዊ ለማድረግ ፈቃደኛ ሆኖ ያለመገኘት፣
5. ህጋዊ አሠራሩን ያልተከተለ ወይም በህጋዊ አሠራር ሽፋን አላማውን የሳተ የውጭ ግንኙነትና ጉዞ ሚፈጸም፤

### 46. የቅጣት አፈጻጸም ሂደት

1. የዚህ መመሪያ አንቀፅ 45 የተላለፈ የስፖርት ማህበር የተፈፀመው ጥፋት ሚኒስቴር መ/ቤቱ አማካኝነት ተጣርቶ በበቂ ማስረጃ ከተረጋገጠ በኋላ ለተገቢው ውሳኔ ለጠቅላላ ጉባኤ እንዲቀርብ ይደረጋል፡፡
2. ጠቅላላ ጉባኤው በአንድ ወር ጊዜ ወስጥ ተሰብስቦ በመሆየት ማህበሩ በአንቀጽ 45 ንዐስ አንቀፅ 1-5 መሠረት ጥፋተኛ መሆኑን ሲያረጋግጥ የጥፋት ደረጃው ከፍተኛ ከሆነ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴውን አሰናብቶ በምትኩ ሌላ ምርጫ ያደርጋል፡፡ ሆኖም የጥፋት ደረጃው ማስተካከል የሚቻል ከሆነ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፡፡
3. ማንኛውም አባል ጥፋተኛ መሆኑ ሲረጋገጥ ይህንን በፈፀመው የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል፣ ፣ጽ/ቤት ኃላፊ እና ሠራተኛ ላይ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው በስነ-ምግባር መመሪያው ማስረት ከጥፋቱ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ እርማጃ ወስዶ ለጠቅላላ ጉባኤው ሪፖርት ያቀርባል፣

### 47. ሚኒስቴሩ፡-

ሀ/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 45 ንዐስ አንቀጽ 2 የተመለከተው ክልከላ በመተላለፍ ተደራጅቶ ለመመዝገብ የቀረበወን ማህበር አይመዘግብም፤ እውቅናም አይሰጥም፡

ለ/ ጠቅላላ ጉባኤው ጉዳዩ በቀረበለት በአንድ ወር ጊዜ ወስጥ ተሰብስቦ ወሳኔ ካልሰጠ የማህበሩን የምዝገባ የምስክር ወረቀት ያግዳል ወይም ይሰርዛል፣

ሐ/ የምዝገባ የምስክር ወረቀት የታገደበት ወይም የተዘረዘረበት ማህበር በማህበሩ ስም ማንኛውም እንቅስቃሴ እንዳያደርግ ያግዳል፣የሚጠወንም ድጋፍ ያቋርጣል፤

መ/ ጠ/ጉባኤው በአንቀፅ 46 ንዑስ አንቀፅ 1-3 መሠረት የሚወሰደው የቅጣት እርምጃ ይከታተላል ሆኖም የተወሰደው እርምጃ ተገቢ ሆኖ ካልተገኘ እገዳ ሊጥል ይችላል፡፡

48. <u>ስለ ማሻሻል</u>

መመሪያወን ማሻሻል አስፈላጊ ስፖርትሆኖ ሲገኝ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በማንቸውም ጊዜ ለሻሻል ይችላል ፡፡

49. <u>የተሻረ መመሪያ</u>

በ2003 ዓ.ም በፌደራል ስፖርት ኮሚሽን የወጣው የስፖርት ማህበራት ስለሚቋቋሙበት ሁኔታ የሚወሰነው መመሪያ በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

50. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በሚኒስትሩ ተፈርሞ ከወጣበት ከ29/01/2011 ዓ.ም.ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**ርስቱ ይርዳ**

**ሚኒስትር**